# የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን

## የተሻሻለው የሃብት ማሳወቅ እና ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ

የካቲት /2013

አዲስ አበባ

# የተሻሻለው የሃብት ማሳወቅ እና ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ

# መመሪያ ቁጥር 18/2013

የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ፣ የምዝገባ መረጃ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እና  የሃብት ምዝገባ መረጃ ለህዝብ ተደራሽ የሚደረግበትን ዝርዝር አሠራር መዘርጋት በማስፈለጉ፣ሃብት የማሳወቅና የማስመዝገብ ግዴታ ለተጣለባቸው የመንግሥት ተሿሚዎች፣የህዝብ ተመራጮች፣ የመንግሥት መስሪያ ቤት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅት እና የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኞች ከሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ጋር በተያያዘ ግዴታቸውን በግልፅነት እና በተጠያቂነት መርህ እንዲወጡ ለማድረግ የሚያስችል ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፣

የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥራን ለማከናወን ሀላፊነት ለተሰጣቸው የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች፣የመንግሥት ልማት ድርጅቶች እና የህዝባዊ ድርጅቶች የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ሥራቸውን በግልፅነት እና በተጠያቂነት መርህ እንዲፈፅሙ ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

ህዝቡ ሃብት የማስመዝገብ ግዴታ ያለባቸው አካላት ላይ ሃብታቸውን በማያሳውቁ ወይም በማያስመዘገቡ ወይም ከገቢያቸው በላይ ወይም አሳንሰው በሚያስመዘገቡ ላይ ሚናውን እንዲወጣ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በሥራላይ ያለውን የሀብት ማሳወቂያና ምዝገባ የአፈፃፀም መመሪያ ከተሻሻለው የፌደራል የሥነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ጋር በተጣጣመ መንገድ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በሀብት ማሳወቅና ማስመዝገብ በወጣው አዋጅ ቁጥር 668/2002 አንቀጽ 24(2) መሰረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. አጭርርዕስ

ይህ መመሪያ "የተሻሻለው የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ፣የሃብት ምዝገባ መረጃ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እና የሃብት ምዝገባ መረጃ ለህዝብ ተደራሽ የሚደረግበትን አሠራር ለማስፈፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 18/2013 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡-

1. **"አዋጅ"** ማለት የሃብት ማሳወቅ እና ምዝገባ አዋጅ ቀጥር 668/2002 ነው፣
2. **"ኮሚሽን ወይም ኮሚሽነር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን እና የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ነው፣
3. **"ሃብት"**ማለት ማንኛውም ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀስ ግዙፍነት ያለው ወይም ግዙፍነት የሌለውን ብረት ሲሆን ይህም የመሬት ይዞታ ፣ህጋዊ የዕዳ ስምምነትን፣ በባንክ ያለ ሃብት፣ ገቢ እና ጥቅም የሚያስገኝ ባለቤትነትን ያካትታል፣
4. **"ሃብት ምዝገባ"**ማለት በሃብት ማሳወቅ እና ምዝገባ አዋጅ አንቀጽ 4 (1) እና (2) በተገለጸው አግባብ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሰረት ሃብት አስመዝጋቢው የራሱንና የቤተሰቡን ሃብት፣ የገቢ ምንጭ የሚያሳውቅበት እና የሚያስመዘግብበት አሠራር ነው፣
5. **"የምዝገባ ዓይነት"** ማለት በኮሚሽኑ ወይም በመንግሥት መስሪያቤት፣ በመንግሥት ልማት ድርጅት እና በህዝባዊ ድርጅት ውስጥ የሚካሄድ የመጀመሪያ፣ የአገልግሎት ማቋረጥ፣የዕድሳት እና የመውጫ ሀብት ምዝገባ ነው፣
6. **"ሃብት የሚያሳውቅ ሰው ወይም ሃብት አስመዝጋቢ"** ማለት በሃብት ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 668/2002 እና በተሻሻ የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ በተደነገገዉ መሰረት ማንኛውም ሃብት የሚያሳውቅና የሚያስመዘገብ ግዴታ ያለበት ማንኛውም ተሿሚ፣ የህዝብ ተመራጭ፣ በመንግሥት መስሪያቤት፣ በመንግሥት ልማት ድርጅት እና በህዝባዊ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ በቋሚነት ወይም በጊዜዊነት ከ3 ወር በላይ ለተራዘመ ጊዜ የሚሰራ ሠራተኛ ነው፡፡

7. **“አግባብነት ያለው የምርመራ አካል”** ማለት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘ ወንጀል መፈጸሙን የሚያመላክት ሁኔታ ሲያጋጥም ጉዳዩን እንዲመረምር የሚመራለት በሕግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ያለው አካል ነው፡፡
8. **“አገልግሎት ማቋረጥ”** ማለት አንድ ሃብት አስመዝጋቢ በመስሪያ ቤቱ ሃብቱን ካስመዘገበ 6 ወር እና ከዛበላይ ሲሰራ ቆይቶ በማንኛውም ሁኔታ መስሪያቤቱን ሲለቅ ሃብት እና የገቢ ምንጬን የሚያስመዘግብበት ሥርዓት ነው፣
9. **“ዋና መዝገብ ወይም ባህር መዝገብ”** ማለት ሃብት ምዝገባ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው የመንግሥት መስሪያቤቶች፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ሃብት ማስመዝገብ ያለባቸውን አስመዝጋቢዎች በሥራ መደብ እና ስም ዝርዝር እንዲይዝ በተለይ የተዘጋጀ ወይም የተደራጀ መረጃ ነው፣
10. **“የሃብት ማሳወቅ እና ምዝገባ አሠራር”** ማለት የሃብት ማሳወቅ እና ምዝገባን፣የሃብት ምዝገባ መረጃ ትክክለኛነት ማረጋገጥን እና የሃብት ምዝገባ መረጃ ለህዝብ ተደራሽ የሚያደረግበትን ሂደት የሚያጠቃልል ተግባር ነው፣
11. **“የሥነምግባር መከታታያ ክፍሎች”** ማለት በመንግሥት መስሪያ ቤት ወይም በመንግሥት ልማት ድርጅቶች ወይም በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ሥራውን በየተቋማቱ ለማሰራት የሚያደራጀቸው አደረጃጀቶች ናቸው፣
12. **“የሃብት ምዝገባ መረጃ ትክክለኛነት ማረጋገጥ”** ማለት በኮሚሽኑ የሃብት ማሳወቅ እና ምዝገባ ዳይሬክቶሬት ሃብት የሚያሳውቀው ግለሰብ የሰጠው መረጃ የተሟላ፣ እውነተኛ፣የአኗኗር ደረጃው ካስመዘገበው ሀብትና የገቢ ምንጭ ጋር፣ የገቢ ሁኔታው ካስመዘገበው ሃብት እና የገቢ ምንጭ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያከናወን ሂደትን የሚመለከት ነው፣
13. **“የሃብት ምዝገባ ትክክለኛነት ቅድመ-ማረጋገጥ”** ማለት በሃብት ምዝገባ ወቅት የሃብት ምዝገባ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ከመሰጠቱ በፊት መረጃው በትክክል እና በተሟላ ሁኔታ ስለመሞላቱ እና በሁሉም ገፆች ላይ የሐብት አስመዝጋቢው ፊርማ ያረፈበት ስለመሆኑ በኮሚሽኑ የሚረጋገጥበት ሂደት ነው፣
14. **“የሃብት ምዝገባ መረጃን ለህዝብ ክፍት ማድረግ”** ማለት በጽሁፍ በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት ተመዝግቦ በኮሚሽኑ እጅ የሚገኝ የሃብት ምዝገባ መረጃ ለሚጠይቅ ሰው ወይም ተቋም ለጠያቂው ተደራሽ የሚደረግበት አሠራር ሲሆን የሚሰጠው መረጃ

በሃብት ማሳወቅና ምዝገባ አዋጅ አንቀጽ12(4) እና በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 13(1) መሠረት በሚስጥር ተጠብቀው እንዲቆዩ የተለዩትን የሃብት አስመዝጋቢውን ቤተሰብ ሃብትና የገቢ ምንጭ መረጃን አይጨምርም፣

15. **"የፌደራል ተቋማት"** ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ የፌደራል መንግስት መስሪያቤቶች እና የፌደራል ልማት ድርጅቶችን ይጨምራል፤

16. **"የመንግሥት መስሪያቤት"**ማለት በጀቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት በጀት የሚተዳደር እና የፌዴራል መንግስቱ ሥራዎች የሚከናወኑበት ማንኛውም መስሪያ ቤት ነው፣

17. **"የመንግሥት ልማት ድርጅቶች"** ማለት የመንግሥት ባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት ማንኛውም የፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅት ወይም የአክሲዮን ኩባንያ ነው፣

18. **"ህዝባዊ ድርጅት"** ማለት በማንኛውም አግባብ ከአባላት ወይም ከህዝብ የተሰበሰበ ወይም ለህዝባዊ አገልግሎት ታስቦ የተሰበሰበ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሌላ ሃብትን የሚያስተዳደር አካልንና አግባብነት ያለው ኩባንያን የሚያካትት የግል ዘርፍ ሲሆን የሃይማኖት ድርጅትን፣የፖለቲካ ድርጅትን(ፓርቲን)፣ የዓለም አቀፍ ድርጅት እና ዕድርንና ተመሳሳይ ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ማህበርን አያካትትም።

19. **"ጥቆማ"** ማለት በሃብት ምዝገባ መረጃ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሂደት ውስጥ ሃብት አስመዝጋቢው ያላስመዘገበው እና የደበቀው ሃብት መኖሩን ወይም ሀሰተኛ የሃብት መረጃ መመዝገቡን አስመልክቶ ከማንኛውም ዜጋ በፅሁፍ በስልክ፣ በቃል፣ በኮሚሽኑ ፋክስ፣ በድረገፅ ወይም በሌላ በማንኛውም መገናኛ ዘዴ የሚሰጥ መረጃ ማለት ነው፣

20. **"ቤተሰብ"**ማለት የተሿሚ፣ የህዝብ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ የትዳር ጓደኛ ወይም በስሩ የሚተዳደር ዕድሜው 18 ዓመት ያልሞላ ልጅ ሲሆን፤ጋብቻ ሳይፈፀም እንደ ባልና ሚስት አብሮ የሚኖር ሰው እና የጉዲፈቻ ልጅን ይጨምራል።

21. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

## 3. የፆታ አገላለፅ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው ለሴት ፆታም ያገለግላል፡፡

## 4. የተፈፃሚነትወሰን

ይህ መመሪያ በፌዴራል ተቋማት ውስጥ ባሉ የመንግሥት መስሪያ ቤት፣የልማት ድርጅት እና ህዝባዊ ድርጅት ውስጥ በሚገኙ ተመራጮች፣ ተሿሚዎች፣ የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ስለ ሃብት ምዝገባ

## 5. ምዝገባ፣የጥቅም ግጭትን መከላከል፣የመረጃ ትክክለኛነት ማረጋገጥና ተደራሽነት

5.1. ኮሚሽኑ ሃብት የመመዝገብ፣ የጥቅም ግጭትን የመከላከልና የማስተዳደር፣ የሃብት ምዝገባ መረጃን ትክክለኛነት የማረጋገጥ፣ መረጃውን በጽሁፍ ለጠየቀ መረጃ ፈላጊ ተደራሽ የማድረግ እና የመጠበቅ/ ማስተዳደር/ ኃላፊነት አለበት፣

5.2. ኮሚሽኑ የሃብት ምዝገባ ሰነዶችን በኃላፊነት ይይዛል፤ይጠብቃል፡፡

## 6. የሃብት ምዝገባ ቅድመ ዝግጅት

6.1. ማንኛውም የፌደራል ተቋማት እና የህዝባዊ ድርጅት ኃላፊ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ አዋጅን በተቋሙ ውስጥ ተፈጻሚ የማድረግ ግዴታ አለበት፣

6.2. ማንኛውም የፌደራል ተቋማት እና የህዝባዊ ድርጅት ኃላፊ በአዋጁ ሃብት እንዲያስመዘግቡ ግዴታ የተጣለባቸውን የህዝብ ተመራጮች፣የመንግሥት ተሿሚዎች፣የመንግሥት መስሪያ ቤት፣የመንግሥት ልማት ድርጅት እና የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኞች እንደተመረጡ፣ እንደተሾሙ፣እንደተመደቡ ወይም እንደተቀጠሩ ሃብታቸውን እንዲያስውቁ የማድረግ ግዴታ አለበት፤

6.3. ማንኛውም የፌደራል ተቋማት እና የህዝባዊ ድርጅት የሰው ሃብት አስተዳደር ሥራ ክፍል በአዋጁና በዚህ መመሪያ ሃብት እንዲያስመዘግቡ ግዴታ የተጣለባቸውን የህዝብ ተመራጮች፣ የመንግሥት ተሿሚዎች፣ የመንግሥት መስሪያ ቤት፣ የመንግሥት ልማት ድርጅት እና የህዝባዊ ድርጅት የሥራ ኃላፊዎች እና

ሠራተኞች እንደተመረጡ፣ እንደተሾሙ፣እንደተመደቡ ወይም እንደተቀጠሩ ሃብታቸውን እንዲያስውቁ ስም ዝርዝራቸውን ለተቋሙ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል የመስጠት ግዴታ አለበት፣

6.4. ማንኛውም የፌደራል ተቋማት እና የህዝባዊ ድርጅት ፋይናንስ ሥራ ክፍል ሃብትና የገቢ ምንጭ የማስመዝገብ እና የማሳወቅ ግዴታ ያለባቸውን የህዝብ ተመራጮች እና የመንግሥት ተሿሚዎች በተሾሙበት ወይም በተመደቡበት ተቋም የመጀመሪያ ወር ደመወዝ ከመከፈሉ በፊት የመጀመሪያ ወይም የዳግም ሃብት ምዝገባ መካሄዱን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፤

6.5. ማንኛውም የፌደራል ተቋማት እና የህዝባዊ ድርጅት የሰው ሀይል አስተዳደር ሥራ ክፍል ሃብትና የገቢ ምንጭ የማስመዝገብ እና የማሳወቅ ግዴታ ያለባቸው የመንግሥት መስሪያ ቤት፣የመንግሥት ልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኞች የቅጥር ደብዳቤ ከመውሰዳቸው በፊት የሃብት ምዝገባ ተግባር እንደ ቅድመ ሁኔታ ተይዞ ሀብት ስለማስመዝገባቸው የሚገልፅ ማስረጃ ከተቋሙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የማቅረብ ግዴታ አለበት፣

6.6. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 6.5 በተደነገገው መሠረት ሃብትና የገቢ ምንጭ የማስመዝገብ እና የማሳወቅ ግዴታ የተጣለባቸውን የፌደራል ተቋማት እና የህዝባዊ ድርጅት ሀብት አስመዝጋቢዎችን ሃብትና የገቢ ምንጫቸውን ሳያስመዘግቡ እና ሳያሳውቁ ሥራ ያስጀመረ የተቋም ኃላፊ እናየሰው ሀብት አስተዳደር ሥራ ክፍል ኃላፊን አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ያደርጋል፣

6.7. ኮሚሽኑ ሃብትና የገቢ ምንጭ የማስመዝገብ እና የማሳወቅ ግዴታ ያለባቸውን የህዝብ ተመራጮች እና የመንግሥት ተሿሚዎች በተሾሙበት ወይም በተመደቡበት ተቋም ሀብታቸውን ሳያስመዘግቡ የመጀመሪያ ወር ደመወዝ የከፈለ የፋይናንስ አስተዳደር ሥራ ክፍል ኃላፊን አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ያደርጋል፣

6.8. ማንኛውም የፌደራል ተቋማት እና የህዝባዊ ድርጅት ኃላፊ እና የሰው ሃብት አስተዳደር ሥራ ክፍል ኃላፊ ከሃብት ማስመዝገብ ጋር ተያያዥነት ያለውን ማንኛውንም የሀብት አስመዝጋቢ የሹመት፣የሕዝብ ተመራጭነት፣ የቅጥር፣ የዕድገት፣ከኃላፊነት የመነሳት፣ ሥራ የመልቀቅ ወይም በጡረታ የመገለል ወቅታዊ ሁኔታዎችን የሚመለከት መረጃ ለሥነምግባር መከታተያ ክፍል የመስጠት ወይም እንዲሰጥ የማድረግ ግዴታ አለበት፣

6.9. ማንኛውም የፌደራል ተቋማት እና የህዝባዊ ድርጅት ኃላፊ እና የሰው ሃብት አስተዳደር ሥራ ክፍል ኃላፊ በቅጥር ወይም በክሊራንስ ቅጹ/ፎርሙ/ ላይ ሃብት አስመዝጋቢው ሃብት ስለማስመዝገቡ የሚገልፅበት ቦታ እንዲኖረው የማድረግ ግዴታ አለበት፣

6.10. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6.9 በተደነገገው መሠረት የተቋሙ ሃላፊዎችና ሠራተኞች በማንኛውም ምክንያት ተቋሙን ሲለቁ ኪሊራንስ ከመውሰዳቸው በፊት ሃብትና የገቢ ምንጫቸውን የማሳወቅና የማስመዝገብና ግዴታ አለባቸው፣

6.11. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6.10 በተደነገገው መሠረት የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች በማንኛውም ምክንያት ተቋሙን ሲለቁ ኪሊራንስ ከመውሰዳቸው በፊት ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ያላደረገ ማንኛውም የፌደራል ተቋማት እና የህዝባዊ ድርጅት ኃላፊ እና የሰው ሃብት አስተዳደር ሥራ ክፍል ኃላፊ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናሉ፣

6.12. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6.10 በተደነገገው መሠረት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ የሥራ ሃላፊዎች እና ሠራተኞች በማንኛውም ምክንያት ሲያገለግሉበት ከነበረው ተቋም ሲለቁ ኪሊራንስ ከመውሰዳቸው በፊት በተቋማቸው በአካል በመቅረብ ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ የማድረግ ግዴታ አለበት፤

## 7. ሀብትና የገቢ ምንጭን ስለማስመዝገብ

7.1. ማንኛውም ሃብት አስመዝጋቢ በራሱ እና በቤተሰቡ አባላት ባለቤትነት ወይም ይዞታ ስር የሚገኘውን ሃብት እና የገቢምንጭ የማስመዝገብና የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

7.2. በጡረታ የተገለለ ወይም ከአንድ የፌደራል ተቋም ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማንኛውም ምክንያት አገልግሎቱን ያቋረጠ ሀብት አስመዝጋቢ ክሊራንስ ከመውሰዱ በፊት ለተቋሙ ሥነምግባር መከታተያ ክፍል በአካል በመቅረብ ሃብቱንና የገቢ ምንጩን የማሳወቅ ግዴታ አለበት፣

7.3. ከአንድ የፌደራል ተቋም ወይም ህዝባዊ ድርጅት ቅርንጫፍ ወደ ሌላ ቅርንጫፍ ወይም ከቅርንጫፍ ወደ ዋና መስሪያቤት እንዲዛወር የተደረገ ማንኛውም ሃብቱን አስቀድሞ ያስመዘገበ ሃብት አስመዝጋቢ የአገልግሎት ማቋረጥ የሃብት ምዝገባ ማድረግ አይጠበቅበትም፣

7.4. ሃብቱን ካስመዘገበ ስድስት ወራት ያልሞላው ማንኛውም ሃብት አስመዝጋቢ ከሚሠራበት ተቋም የለቀቀ እንደሆነ የአገልግሎት ማቋረጥ ምዝገባ ማድረግ አይጠበቅበትም፡፡

7.5. ሃብት አስመዝጋቢው ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ ከሆነ ሃብት የማስመዝገብ ግዴታ አይኖርበትም፡፡ ይህም ለእዳ እገዳ ነፃ ማረጋገጫ /ክሊራንስ/ ማቅረብንና መሰል ግዴታዎችን ይቀሩለታል፣

7.6. ማንኛውም ሃብት አስመዝጋቢ ከክልል ተዛውሮ በፌደራል ተቋም ሲሾም ወይም ሲመደብ የሀብት ምዝገባ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

7.7. የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የተመዘገበውን የሀብት ምዝገባ ሰነድ ምዝገባው በተጠናቀቀ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ የማስረከብ ግዴታ አለበት፣

7.8. የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ በሁሉም የምዝገባ አይነት ገቢ ለአደረጋቸው የሃብት ምዝገባ ሰነዶች የሃብት ምዝገባ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከኮሚሽኑ በመረከብ ሃብታቸውን ላስመዘገቡ ለተቋሙ ሀብት አስመዝጋቢዎች የመስጠት ግዴታ አለበት፣

7.9. የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተሰጣቸው ኃላፊነት መሠረት የሀብት ምዝገባ ሥራ ሲያካሂዱ በሥራው አጋጣሚ ያወቁትን ማንኛውንም የሃብት ምዝገባ መረጃዎችን ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፣

## 8. የሃብት ምዝገባና የቀነ ገደብን ስለማራዘም

8.1. የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ሁሉንም የምዝገባ አይነቶች ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲካሄዱ የማድረግ ግዴታ አለበት፤

8.2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ 8.1 መሰረት ሃብታቸውን በተገለፀው ቀነ-ገደብ ቀርበው ያላስመዘገቡ ሃብት አስመዝጋቢዎችን የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ስም ዝርዝራቸውን በማስታወቂያ ሰሌዳ ወይም በሌላ አመች ዘዴ ያሳውቃል፡

8.3. የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ 8.2 በወጣው ማስታወቂያ መሠረት ሀብት አስመዝጋቢዎች ሀብታቸውን ሳያስመዘግቡ የቆዩበትን አሳማኝ ምክንያት ካላቸው ይህንኑ የሚገልፅ ማስረጃ በጽሑፍ አያይዘው እንዲያቀርቡ ያደርጋል፤

8.4. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ 8.3 እንደተደነገገው ማስረጃውን ያላቀረቡ ሀብት አስመዝጋቢዎች በአንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ1 መሠረት የ1,000 ብር (አንድ ሺ ብር)

የገንዘብ ቅጣት ከፍለው የባንክ ዋና ስሊፕ ደረሰኝ በማቅረብ በ10 ቀናት ውስጥ ሀብታቸውን ያስመዘግባሉ፤ የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የባንክ ዋና ስሊፕ ደረሰኝ በመሰብሰብ ለኮሚሽኑ የፋይናንስ ክፍል ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት፣

8.5. ከዚህ በላይ በአንቀፅ 8.4 የተደነገገው እንተጠበቀ ሆኖ ሃብት አስመዝጋቢው ለተወሰነ ጊዜ ታሞ የቆየ ከሆነ እና ሕመሙ በሐኪም በተረጋገጠ የህክምና ማስረጃ የተደገፈ ከሆነ ወይም ሃብት አስመዝጋቢው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ማለትም በእስር፣በሀዘን፣በወሊድ ምክንያት፣ ለሥራ ጉዳይ ወይም ለስልጠና ወደ ውጭ ሀገር በመሄዱ ወይም በሀገር ውስጥ ሥልጠና ምክንያት ከመደበኛ የሥራ ገበታው ውጭ ሆኖ የቆየ ከሆነ ህጋዊ የሆነ ማስረጃውን በማቅረብ ያለቅጣት ሀብቱን እንዲያስመዘግብ ይደረጋል።

8.6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 8.4 መሠረት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ የገንዘብ ቅጣት ተቀጥቶ በ10 ቀናት ውስጥ ሀብቱን ሳያስመዘግብየቀረን ማንኛውም ሀብት አስመዝጋቢ ስምና የሥራ ሃላፊነት ጠቅሶ ለተቋሙ ሃላፊ በማሳወቅ ለኮሚሽኑ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፣

8.7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 8.6 መሰረት ኮሚሽኑ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ቅጣቱን ከፍሎ ሳያስመዘግብ የቀረን ሀብት አስመዝጋቢ በሕግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ለተሰጠው አካል ያስተላልፋል።

## 9. የሀብት ምዝገባ ትክክለኛነት ቅድመ ማረጋገጥ

9.1. የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ሀብት አስመዝጋቢው በአካል በመቅረብ በህጋዊ ቅፅ በግልፅ ያለብልሽት መሙላቱን፣ በእያንዳንዱ ቅጽ፣ገጽ እና በገፁ መጨረሻ ላይ መፈረሙን አረጋግጦ የመረከብ ግዴታ አለበት።

9.2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 9.1 በተደነገገው መሰረት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ አረጋግጦ የተረከበውን የሀብት ምዝገባ ቅፅ በአንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 7 መሠረት በ10 ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ ገቢ ያደርጋል/ያስረክባል።

9.3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 9.2 በተደነገገው መሰረት ኮሚሽኑ የተረከበውን የመጀመሪያ ወይም የዕድሳት ቅፅ በትክክል መሞላቱን ሲያረጋግጥ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ የሀብት ምዝገባ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት ግዴታ አለበት፣

9.4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 9.1 ላይ የተጠቀሱት አንድ ወይም ከዚያ በላይ መስፈርቶች ያልተሟሉ ከሆነ ኮሚሽኑ ያልተሟሉ መረጃዎችን በዝርዝር በመጥቀስ እንዲስተካከሉ ቅፁ ከኮሚሽኑ ጽ/ቤት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ባሉት 3 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለተቋሙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የመመለስ ግዴታ አለበት፣

9.5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 9.4 መሠረት እንዲስተካከሉ ለተቋምየሥነምግባር መከታተያክፍል ተመላሽ የተደረገ የሀብት ምዝገባ ቅጽ በሀብት አስመዝጋቢ ተቋም ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 የሥራ ቀናት ውስጥ መረጃው ተሟልቶ ለኮሚሽኑ ገቢ መደረግ አለበት፣

9.6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 9.5 መሠረት የሥነምግባር መከታታያ ክፍሉ መረጃውን በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያላስተካከለ የሃብት አስመዝጋቢ ሃብቱን እንዳላስመዘገበ ወይም እንዳላሳወቀ በመቁጠር ስም ዝርዝሩን ለተቋሙ ሃላፊ በማሳወቅ ለኮሚሽኑ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፣

9.7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 9.6 መሠረት ሀብት ያላስመዘገበው ሃላፊ ወይም ሠራተኛ ዝርዝር የደረሰው የተቋም ወይም የህዝባዊ ድርጅት ኃላፊ በአንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የተቋሙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በድጋሚ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሀብት አስመዝጋቢው ሃብቱን እንዲያስመዘግብ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

# 10. ሃብትን አለማስመዝገብ የሚያስከትለው ቅጣት

10.1.ማንኛውም ሀብት አስመዝጋቢ በመደበኛው ወይም በተራዘመለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ሃብቱን ሳያስመዘግብ ከቀረ ለኮሚሽኑ ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር) ቅጣት ይከፍላል፣

10.2. ሀብት አስመዝጋቢው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ1 የተጠቀሰውን የገንዘብ ቅጣት ለማስፈፀም የተላለፈው ውሳኔ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት 5 ቀናት ውስጥ ቅጣቱን መክፈል አለበት፣

10.3. ሀብት ባለማስመዝገብ የሚከፈል ቅጣት ሀብት የማስመዝገብን ግዴታ አያስቀርም፡፡

10.4 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 10.1 መሠረት የሥነምግባር መከታታያ ክፍል በተሰጠው ጊዜ ውስጥ የሃብት ምዝገባ ቅጹን ሞልቶ ያላስረከበን ሀብት አስመዝጋቢ ስምና የሥራ

ድርሻ በመጥቀስ ለተቋሙ ሃላፊ በማሳወቅ ለኮሚሽኑ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፣

10.5 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 10.2 መሠረት ሃብት አስመዝጋቢው በተሰጠው 5 የሥራ ቀናት ውስጥ የሃብት ምዝገባ ቅጹን ሞልቶ ማስረከብ ካልቻለ ተጠያቂ እንዲሆን ኮሚሽኑ በሕግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ላለው አግባብነት ላለው አካል ያስተላልፋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የሃብት ምዝገባ መረጃን ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ

### 11. የሃብት ምዝገባን ትክክለኛነት ማረጋገጥ

11.1ኮሚሽኑ ከሚከተሉት አንዱ ወይም ከአንድ በላይ ምክንያት/ሁኔታ ሲኖር በማንኛውም የሀብት አስመዝጋቢ መረጃ ላይ የመረጃ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ተግባር ያከናውናል፡-

ሀ. የቀረበው መረጃ ያልተሟላ ከሆነ፣

ለ. ሀብት አስመዝጋቢው ሀብት ለማስመዝገብ ከሚገባው በላይ የዘገየ ወይም በምዝገባ ሂደት የመረበሽ፣ያለመረጋጋት፣መረጃ ወይም ሃሳብ የመቀያየር ምልክቶች ሲያሳይ፣

ሐ. የቀረበው መረጃ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መሆኑን ለመጠራጠር የሚያስችል በቂ ምክንያት ካለ፣ (በህጋዊ ገቢውና በአስመዘገበው ሀብት መካከል በግልጽ የሚታይ ከፍተኛ መራራቅ ወይም ማነስ ወይም መብለጥ ሲኖር)፣

መ. የቀረበው መረጃ በምዝገባው ትክክለኛነት ላይ ጥያቄ በሚያነሳ ሦስተኛ ወገን ወይም በጠቋሚ በኩል ጥቆማ ሲቀርብ፣

ሠ. ከሙስና ጋር የተያያዘ የምርመራ ሂደት እየተካሄደበት ከሆነ፣

ረ. ኮሚሽኑ በሙስና ተጋላጭነታቸው በጥናት በለያቸው የፌደራል ተቋማት ወይም ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ ሃብት አስመዝጋቢዎች ሆነው ሲገኙ፣

ሰ. ኮሚሽኑ በትኩረት መስክ በለያቸው የፌደራል ተቋማት ወይም ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ሃብት አስመዝጋቢዎች ሆነው ሲገኙ፣

ሸ. ከፖለቲካ አንጻር የያዙት ቦታ ትኩረት የሚስብ ሆኖ ሲገኝ፣

ቀ. በዚህ አንቀጽ 11 (1) (ከሀ-ሸ) በተጠቀሱት ምክንያቶች/ ሁኔታዎች የሚጣራ መረጃ በበቂ መጠን ባለመገኘቱ ኮሚሽኑ የሀብት ምዝገባ መረጃን ትክክለኛነት የማረጋገጥ መደበኛ ሥራ ለመሥራት ወስኖ የአስመዝጋቢው የሀብት ምዝገባ መረጃ በናሙና ምርጫ የተመረጠ ሆኖ ሲገኝ ይሆናል፡፡

**11.2 በመረጃ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሂደት ወቅት ኮሚሽኑ፡-**

ሀ.ሃብት አስመዝጋቢው በሞላው የሃብት ምዝገባ ቅጽ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ መረጃ እና ማብራሪያ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል፣

ለ. የሃብት አስመዝጋቢውን መረጃ የያዘ ማንኛውም ባንክ፣የገንዘብ ተቋም ወይም ሌላ ድርጅት/ሰው/ የያዘውን የሃብት መረጃ እንዲሰጥ ሊያዝ ይችላል፣

ሐ. ዋና ኦዲተርን ወይም ማንኛውንም አግባብነት ያለው አካል ሙያዊ ድጋፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**11.3 ኮሚሽኑ በመረጃ ትክክለኛት ማረጋገጥ ሂደት ግኝቱ ጥቃቅን የመረጃ ስህተት ከሆነ ከሚከተሉት እርምጃዎች አንዱን ጥቅም ላይ ሊያውል ይችላል፡-**

ሀ. ለመጀመሪያ ጊዜ ለተፈፀመ ጥቃቅን የመረጃ ስህተት ለሃብት አስመዝጋቢው የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፣

ለ. ሃብት አስመዝጋቢው ለሁለተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ስህተት ከፈጸመ ብር 1,000 (አንድ ሺህብር) የገንዘብ ቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል፣

ሐ. ሃብት አስመዝጋቢው ለ3ኛ ጊዜ ተመሳሳይ ስህተት ከፈፀመ ጉዳዩ በሕግ የመመርመር ስልጣን ላለው አካል ይላካል፡፡

11.4 ኮሚሽኑ የሃብት ምዝገባ መረጃ ማጭበርበር ተፈጥሯል ወይም ሆነ ተብሎ አሳሳች መረጃ ተሰጥቷል ወይም እውነቱን ለመደበቅ ተሞክሯል ብሎ በሚያምንበት በማናኛውም ጊዜ ምርመራ እንዲደረግ እና ተጠያቂ እንዲሆን በሕግ የመመርመረና የመክሰስ ስልጣን ለተሰጠው አካል ያስተላልፋል፡

## 12. የአኗኗር ሁኔታ ወይም ደረጃ ማረጋገጥ

በሀብት አስመዝጋቢው የኑሮ ደረጃ እና እርሱ እና/ ወይም የቤተሰቡ አባላት በሚያገኙት ገቢ መካከል ያለውን መጣጣም ለማረጋገጥ ኮሚሽኑ የአኗኗር ሁኔታቸው ላይ ማጣራት ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## የሃብት ምዝገባ መረጃ ለህዝብ ክፍት /ተደራሽ/ ስለሚሆንበት ሁኔታ

### 13. የሃብት ምዝገባ መረጃን ለህዝብ ክፍት /ተደራሽ/ ስለማድረግ

13.1 ኮሚሽኑ የሃብት ማሳወቂያ ቅጽ ውስጥ ተመዝግበው ያሉ መረጃዎች በሙሉ ተደራሽ ሊያደረግ ይችላል ወይም ይሰጣል፡፡ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል የግል ሚስጥራዊ መረጃዎች የሚባሉት የስልክ ቁጥር፣የባንክ ሒሳብ ቁጥር እና የመኖሪያ አድራሻ ናቸው፣

13.2 በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም መረጃዎቹ በፍትህ አካላት ሲጠየቁ ወይም እንደ ሁኔታው ኮሚሽኑ ለሌሎች ዓላማዎች እንዲውሉ ሲወስን የግል ሚስጥራዊ /ግላዊ/ መረጃዎችም ሊገለጹ ይችላሉ፣

13.3 ማንኛውም የሃብት ምዝገባ መረጃ እንዲሰጠው የሚፈልግ ሰው ጥያቄውን በጽሁፍ ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት፣

13.4 ኮሚሽኑ የቀረበለትን የመረጃ ጥያቄ በመቀበል በኮሚሽኑ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ መሰረት ለጠያቂው ሰው ተገቢውን መረጃ ይሰጣል፣

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 14. ስለ ቅጣት ገንዘብ አሰባሰብ

14.1የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ሃብት አስመዝጋቢዎች ሀብታቸውን ባለማስመዝገባቸው ወይም በምዝገባ ሂደት በፈፀሙት ግድፈት የሚከፍሉትን ቅጣት በኮሚሽኑ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሂሣብ ቁጥር 1000001844532 ወይም ኮሚሽኑ ወደፊት በሚያሳውቀው የሂሳብ ቁጥር ገቢ በማድረግ ዋናውን የባንክ ስሊፕ ደረሰኝ ለኮሚሽኑ የግዥ፣ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ያቀርባሉ፣

14.2 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 14.1 መሠረት የኮሚሽኑ የግዥ፣ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የባንክ ዋናው ስሊፕ/ደረሰኝ/ እንደደረሰው የገቢ ደረሰኝ በመቁረጥ ለተቀጭው ይሰጣል፣

14.3 የኮሚሽኑ የግዥ፣ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቅጣት ከከፈሉ ሃብት አስመዝጋቢዎች የተረከበውን ዋናው ስሊፕ/ደረሰኝ/ በማደራጀት መረጃውን ይይዛል፡፡ በሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ዳይሬክቶሬት በተጠየቀ ጊዜ መረጃውን የመስጠት ግዴታ አለበት፣

14.4 የኮሚሽኑ የግዥ፣ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ 14.1 እና 14.2 መሠረት ገቢ የተደረገውን የቅጣት ገንዘብ ከዋናው ስሊፕ/ደረሰኝ/ ጋር በማስታረቅ በየወሩ ለገንዘብ ሚኒስቴር ፈሰስ ያደርጋል፡፡ ስለ አፈፃፀሙም ለሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ዳይሬክቶሬት ያሳውቃል፡፡

## 15. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው የሃብት ማሳወቅና ማስመዝገብ አዋጅ ቁጥር 668/2002 እና አዋጁን ለማስፈፀም የወጣውን ይህን የአፈፃፀም መመሪያ ኮሚሽኑ በሚያስፈፅምበት ወቅት መረጃ የመስጠትና የመተባበር ህጋዊ ግዴታ አለበት፡፡

## 16. ስለቅጣት

የሀብት ምዝገባ አዋጅንና አዋጁን ሥራ ላይ ለማዋል የወጣውን ይህንን መመሪያ በመፈጸም ሂደት ላይ የመተባበር ህጋዊ ግዴታዉን ያልተወጣ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው የወንጀል ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 17. የቅሬታአቀራረብ

17.1 ማንኛውም አገልግሎት ጠያቂ በተሰጠው አገልግሎት ላይ ቅሬታ ካለው ቅሬታውን አገልግሎቱን ለሰጠው የሥነምግባር መከታታያ ክፍሉ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

17.2 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 17.1 በተደነገገው መሠረት ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ምላሽ ያልረካ ከሆነ ለመስሪያ ቤቱ፣ ለፌደራል ተቋሙ ወይም ለህዝባዊ ድርጅቱ ኃላፊ ቅሬታውን ያቀርባል፡፡

17.3 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 17.1 በተደነገገው መሠረት የተቋሙ ኃላፊ የሠጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## 18. መመሪያዉን ስለማሻሻል

ኮሚሽኑ ይህንን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 19. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረዉም፡፡

## 20. ስለተሻረ ሕግ

የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን የተሻሻለው የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 13/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 21. መመሪያዉ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከየካቲት 8 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ፤የካቲት 8 ቀን2013 ዓ.ም**

**ፀጋ አራጌ**

**የፌዴራልየሥነምግባርናየፀረ-ሙስናኮሚሽንኮሚሽነር**